- ሰይጣን የሚጠላው ማንን ነው?

- ሰይጣን የሚጠላው እግዚአብሔርንና ሰዎችን ሁሉ ነው።

- ሰይጣን እግዚአብሔርን ይጠላል የእግዚአብሔርንም ሥራ ሊያፈርስ ይሞክራል።

- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ይጠላል ሰዎችን ሁሉ ሊያጠፋም ይሞክራል።

- ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ ይፈልጋል?

- አይፈልግም።

- ሰይጣን እናንተ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳትሰሙ የሚፈልገው ለምንድን ነው?

- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላና ወደ ዘላለሙ የእሳት ባሕር እንዲጣሉ ስለሚፈልግ ነው።

- የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰሙ ከዘላለሙ የእሳት ባሕር እንዴት ማምለጥ እንደሚቻል ትማራላችሁ።

- የእግዚአብሔርን ቃል የማትሰሙ ከሆነ ከዘላለሙ የእሳት ባሕር እንዴት ማምለጥ እንደሚቻል ማወቅ አትችሉም።

- እግዚአብሔር ቃሉን እንድትሰሙ ይፈልጋል።

- ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ አይፈልግም።

- የእግዚአብሔርን ቃል እንደምትሰሙ ተስፋ አደርጋለሁ።



## ትምህርት 11

- በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን የት ይኖሩ ነበር?
- በዔድን ገነት ውስጥ።

- አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት ውስጥ ሳሉ እንዴት ነበሩ?
- አዳምና ሔዋን በጣም ደስተኞች ነበሩ።

- አዳምና ሔዋን በጣም ደስተኞች የነበሩት ለምንድን ነው?

- አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ስለነበራቸው።
- አዳምና ሔዋን የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ስለ ነበሯቸው።

- ያን ጊዜ የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ሰይጣን የት ነበረ?

- ሰይጣን እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሲፈጥር ይመለከት ነበር።

- ሰይጣን እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በራሱ አምሳል እንደፈጠረው ስላወቀ፥ እጅግ ተበሳጨ።

- ሰይጣን እግዚአብሔር አዳምን በምድር ላይ ገዢ እንዳደረገው ስላወቀ እጅግ ተበሳጨ።

- ሰይጣን እግዚአብሔርን ይጠላል።
- ሰይጣን እግዚአብሔርን ማሸነፍ እንደማይችል ያውቃል።

- ስለዚህ ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ለማሸነፍ ወሰነ።
- ስለዚህ ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ለማጥፋት ወሰነ።

- ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን ለማጥፋት እንዴት እንደ ሞከረ ተመልከቱ።

ዘፍጥረት 3፡1

1- እባብ እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው የዱር አራዊት ሁሉ ተንኰለኛ ነበረ፤ ሴቲቱንም፣ «በእርግጥ እግዚአብሔር በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ ብሎአልን?» አላት።

- ከሔዋን ጋር የተነጋገረ ው በእርግጥ እባ ብ ነበር?
- አልነበረም።

- ታዲያ ከሔዋን ጋር የተነጋገረው ማን ነበረ?
- ሰይጣን።

- ሔዋን ከእርሷ ጋር ይነጋገር የነበረው ሰይጣን እንደሆነ ታውቅ ነበር?
- አታውቅም።

- ሰይጣን በእባቡ ውስጥ ገብቶ ነበር።
- ሰይጣን በእባቡ ውስጥ የገባው ለምንድን ነው?

- ራሱን ለመደበቅ ነው።

- ሰይጣን በእባቡ ውስጥ የተደበቀው ለምንድን ነው?

- ሔዋንን ሊያጠምድ ስለ ፈለገ ነው።
- ሔዋንን ሊያስት ስለ ፈለገ ነው።
- ሔዋንን ሊያጠፋት ስለ ፈለገ ነው።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡



- የቅጠል ልብስ ሠሩ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ከሠሩ በኋላ እግዚአብሔር ሊጐበኛቸው ወደ እነርሱ ሲመጣ ምን አደረጉ?

- ከእግዚአብሔር ተደበቁ።

- ከእግዚአብሔር መደበቅ ይቻላል?
- አይቻልም።

- ከእግዚአብሔር መደበቅ የማይቻለው ለምንድን ነው?
- እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ስለሚገኝ።

- ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ወዳጆች ነበሩ?
- አሁን ግን አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆኑ።

- ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ልጆች ነበሩ።
- አሁን ግን አዳምና ሔዋን የሰይጣን ልጆች ሆኑ።

- ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ነበራቸው።
- አሁን ግን አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ተደበቁ።

- ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ተከተሉ።
- አሁን ግን አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ተከተሉ።

- ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን ክፉን አያውቁም ነበር።
- አሁን ግን አዳምና ሔዋን ክፉን አውቀዋል።

- ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን አያፍሩም ነበር።
- አሁን ግን አዳምና ሔዋን አፍረዋል።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ስለታዘዙ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆኑ።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- አንድ ወዳጃችሁ እናንተን ትቶ ሊገድላችሁ ከሚፈልግ ጠላታችሁ ጋር ቢተባበር፥ ያ ወዳጃችሁ የእናንተ ጠላት ሆነ ማለት ነው አይደል?

- አዎን።

- አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር በመለየታቸው፥ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነዋል።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ስለ ተከተሉ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነዋል።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩ በኋላ ሌላ ምን ደረሰባቸው?

ዘፍጥረት 3፡7-8

7- የሁለቱም ዐይኖች ተከፈቱ፤ ዕራቍታቸውን መሆናቸውንም ተገነዘቡ። ስለዚህ የበለስ ቅጠል ሰፍተው አገለደሙ።

8- ቀኑ መሸትሸት ሲል፣ እግዚአብሔር አምላክ በአትክልቱ ስፍራ ሲመላለስ አዳምና ሔዋን ድምፁን ሰምተው ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በዛፎቹ መካከል ተሸሸጉ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ካደረጉ በኋላ ምን ተገነዘቡ?
- ዕራቁትነታቸውን ተገነዘቡ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ከሠሩ በኋላ ዕራቁት መሆናቸውን ሲገነዘቡ፥ ምን አደረጉ?



- አዳኝ አንድን አውሬ ለማጥመድ ከፈለገ አውሬው ወጥመድ ውስጥ እንዲገባለት ራሱን ይሰውራል?

- አዎን።

- ራሱን ባይሰውር ምን ይሆናል?
- አውሬው ወጥመድ ውስጥ አይገባም።

- አዳኝ አውሬ ለማጥመድ ራሱን እንደሚሰውር ሁሉ ሰይጣንም ሔዋንን ለማጥመድ ራሱን ሰወረ።

- ዛሬም፥ ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድና ለማሳት እየሞከረ ነው?
- አዎን።

- ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድና ለማሳት የሚሞክረው እንዴት ነው?

- ሰይጣን የሚጠቀምበት አንደኛው መንገድ፥ በልባችን ውስጥ ለእኛ በመናገር ነው።

- ሰይጣን የሚጠቀምበት ሁለተኛው መንገድ በሌሎች ሰዎች በኩል ለእኛ በመናገር ነው።

- ሰይጣን የሚጠቀምበት ሦስተኛው መንገድ በአጋንንቱ በኩል ለእኛ በመናገር ነው።

- ሰይጣን የሚጠቀምበት አንደኛው መንገድ፥ በልባችን ውስጥ ለእኛ በመናገር ነው።

- አንዳንዴ ሰይጣን የእርሱን አሳብ በልባችን ውስጥ ያስቀምጣል።

- እኛም እንዲህ ያሉት አሳቦች የራሳችን ይመስሉናል ነገር ግን እነዚህ አሳቦች ሰይጣን በልባችን ውስጥ ያስቀመጣቸው የእርሱ አሳቦች ናቸው።

- ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳታምኑ ይነግራችኋል።

- እንደዚህ ያሉት አሳቦች ከእግዚአብሔር አይደሉም።
- እንዲዚህ ያሉትን አሳቦች በልባችሁ ውስጥ ያስቀመጠው ሰይጣን ነው።

- ሰይጣን የሚጠቀምበት ሁለተኛው መንገድ በሌሎች ሰዎች በኩል ለእኛ በመናገር ነው።

- ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዳትሰሙ ሊነግሯችሁ ይችላሉ።

- ያ አሳብ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።
- ያ አሳብ ሰይጣን በሌላው ሰው ልብ ውስጥ ያስቀመጠው አሳብ ነው።

- ሌሎች ሰዎች እንዲህ ሊሏችሁ ይችላሉ፡- «እኛ የራሳችን ሃይማኖት አለን። ስለዚህ እነዚህን አዳዲስ ሃይማኖቶች አንፈልግም» ሊሉ ይችላሉ።

- ያ አሳብ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።
- ያ አሳብ ሰይጣን በሌሎች ሰዎች ልብ ውስጥ ያስቀመጠው አሳብ ነው።

- ሰይጣን የሚጠቀምበት ሦስተኛው መንገድ በአጋንንቱ በኩል ለእኛ በመናገር ነው።

- አጋንንት ለቀድሞ አባቶቻችሁ ተናግረዋል።

- አጋንንት የቀድሞ አባቶቻችሁ ልጆቻቸውን በእሳት እንዲያቃጥሉ ነግረዋቸዋል እነርሱም አድርገውታል።



- አሁን ደግሞ ሰይጣን ሔዋን እግዚአብሔርን እንዳትታዘዝ ለማድረግ ፈለገ።

- እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው ሰዎች እንደፈለጉ እንዲኖሩ አይደለም።

- እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ሆነው እንዲኖሩ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው በራሳቸው ሕግ እንዲኖሩ አይደለም።
- እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው በእግዚአብሔር ሕግ እንዲኖሩ ነው።

- ሔዋን ምን ያደረገች ይመስላችኋል?
- ሔዋን እግዚአብሔርን ወይስ ሰይጣንን ታዘዘች?

ዘፍጥረት 3፡6

6- ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ።

- ሰይጣን ሔዋንን አሳታት ሔዋንም ሰይጣን የነገራትን አመነች።
- ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ብላ ከፍሬው በላች።

- አዳምም ደግሞ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ብሎ ከፍሬው በላ።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣን የነገራቸውን ሰሙ
- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር የነገራቸውን አልሰሙም።

- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ አሉ።
- አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠሩ።

- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ስላሉ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆኑ።

- እንደሚሞቱ።

- ሰይጣን ለሔዋን መልካምንና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከበሉ ምን እንደሚሆኑ ነገራት?

- እንደማይሞቱ።
- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ፍሬዋን ከበሉ እንደሚሞቱ ተናገረ።

- ሰይጣን አዳምና ሔዋን ፍሬዋን ቢበሉ እንደማይሞቱ ተናገረ።

- እውነቱን የተናገረው ማን ነበር? እግዚአብሔር ወይስ ሰይጣን?
- እግዚአብሔር ነው።

- ሰይጣን እግዚአብሔርን ምን ብሎ ጠራው?
- ሰይጣን እግዚአብሔርን «ውሸታም» ብሎ ጠራው።

- ሰይጣን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከበሉ ሌላ ምን ይሆናል አለ?

- እንደ እግዚአብሔር እንደሚሆኑ።

- ሰዎች እንደ እግዚአብሔር መሆን ይችላሉ?
- አይችሉም።

- አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው።
- ሰይጣን ሔዋን እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆን የነገራት ዋሽቶ ነው።

- በመጀመሪያ ሰይጣን እግዚአብሔርን አልታዘዝ አለ።



- ያ አሳብ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።

- ያንን አሳብ በቀድሞ አባቶቻችሁ ልብ ውስጥ ያስቀመጡት ሰይጣንና አጋንንቱ ናቸው።

- ሔዋን እያነጋገራት ያለው ሰይጣን መሆኑን ታውቅ ነበር?
- አላወቀችም።

- ሔዋን እያነጋገራት ያለው ሰይጣን መሆኑን አላወቀችም ነበር።
- ምክንያቱም ሰይጣን ራሱን ሰውሮ ነበር።

- የቀድሞ አባቶቻችሁ የተናገራቸው ሰይጣን መሆኑን አያውቁም ነበር።
- ምክንያቱም ሰይጣን ራሱን ሰውሮ ነበር።

- ሰይጣን ሔዋንን ለማጥመድና ለማሳሳት ራሱን ሰወረ።
- ሰይጣን የቀድሞ አባቶቻችሁን ለማጥመድና ለማሳሳት ራሱን ሰወረ።

- ሰይጣን ሔዋንን ለማጥመድና ለማሳሳት የፈለገው ለምንድን ነው?

- ሰይጣን ሔዋንን ስለ ጠላ ነው።
- ሰይጣን ሔዋንን ማጥፋት ስለ ፈለገ ነው።

- ሰይጣን የቀድሞአባቶቻችሁን ለማጥመድና ለማሳሳት የፈለገው ለምንድን ነው?

- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላ ነው።
- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ለማጥፋት ስለሚፈልግ ነው።

- እስቲ ሰይጣን ሔዋንን የጠየቃትን ጥያቄ ደግመን እንመልከት።

## ዘፍጥረት 3፡1

1-ሰይጣን ሴቲቱንም፣ በእርግጥ እግዚአብሔር በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ ብሎአልን» አላት።

- ሰይጣን ሔዋንን ይህን ጥያቄ የጠየቃት ለምን ነበር?
- ሰይጣን እግዚአብሔር የተናገረውን ያውቃል።

- ሰይጣን እግዚአብሔር «መልካምና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብሉ» እንዳላቸው ያውቃል።

- ሰይጣን ሔዋንን ይህን ጥያቄ ለምን ጠየቃት?

- ሰይጣን ሔዋንን ይህን ጥያቄ የጠየቃት ሊያጠምዳት ነው።
- ሰይጣን ሔዋንን ይህን ጥያቄ የጠየቃት ሊያስታት ነው።
- ሰይጣን ሔዋንን ይህን ጥያቄ የጠየቃት ሊያጠፋት ነው።

- የሔዋንን መልስ እናንብብ፡

## ዘፍጥረት 3፡2-3

2- ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለችው፤ «በአትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት እንችላለን፤

3- ነገር ግን እግዚአብሔር <በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ ትሞታላችሁ> ብሎአል።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን የዛፉን ፍሬ እንዳይነኩ አላለም።
- እግዚአብሔር የተናገረው አዳምና ሔዋን ፍሬውን እንዳይበሉ ነው።



- ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው እግዚአብሔር ከዛፉ ፍሬ እንዳይበላ ያዘዘው አዳምን ብቻ ነበር።

- ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ትእዛዝ ለሔዋንም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።

- የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው ከረጅም ዘመናት በፊት ለኖሩ ሰዎች ቢሆንም የተጻፈው ደግሞ ዛሬ ለምንኖረው ለእኛም ነው።

- እግዚአብሔር ለጥቁር ሕዝብ አንድ መልእክት ለነጭ ሕዝብ ደግሞ ሌላ መልእክት የለውም።

- እግዚአብሔር አንድ መልእክት ለአፍሪካውያን ሌላ መልእክት ለአውሮፓውያን የለውም።

- የእግዚአብሔር መልእክት ለሁሉም ሰዎች አንድ ዓይነት ነው።
- የእግዚአብሔር መልእክት ትላንትም ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው።

- ሰይጣን ለሔዋን ምን የ ሚል መልስ የሰጣት ይመስላችኋል።

## ዘፍጥረት 3፡4-5

4- እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ «መሞት እንኳ አትሞቱም።

5- ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ዐይናችሁ እንደሚከፈትና መልካምና ክፉን በማወቅ፣ እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው።»

-እግዚአብሔር ለአዳም መልካምና ክፉ ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከበሉ ምን እንደሚሆኑ ነገረው?